# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)


**<u>ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት የተሰጠ ወቅታዊ መግለጫ</u>**

**<u>በኃይልና በሸፍጥ የተጭበረበረው የምርጫ ሂደት በሕጋዊ መንገድ መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡</u>**

"እንከን የለሽ አደርገዋለሁ" ተብሎ በኢሕአዴግ አመራር ብዙ የተወራለት የ1997 ዓ/ም የተወካዮች ምክር ቤትና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ አጀማመሩ በመጠኑም ቢሆን ከቀድሞው የተሻለ ቢሆንም አጨራረሱ እንደተለመደው ኢሕአዴግ ከቀድሞው በባሰ ሁኔታ ገሃድ የወጣ ማጭበርበርና ሌሎች ሕገ-ወጥ እርምጃዎች ውስጥ የገባበት ሆኗል፡፡ በሕዝባችን ሙሉ ተሳትፎ የተሟሟቀው ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ በሂደት ላይ እያለ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ በታወጀው ሕገ-ወጥ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አማካይነት ሂደቱን ለማጨናገፍ እየተሞከረ ይገኛል፡፡

ከዚያም በመቀጠል እስከ ምርጫው ማግስት ድረስ በታየው የሽንፈት ውጤት እጅግ የተደናገጠው የኢሕአዴግ አመራር የምርጫው ውጤት ቆጠራ ግማሹ ያህል እንኳ ባላለቀበት ሁኔታ "በምርጫው አሸንፌአለሁ፥ የፌዴራሉንና የክልል ምክር ቤቶችን ለመቆጣጠር ከሚያስፈልገኝ ውጤት የበለጠ አግኝቻለሁ" ብሎ በሚቆጣጠራቸው የመገናኛ ብዙሓን ሁሉ በማወጅ ቆጠራው ትርጉም የለሽ እንዲሆንና በበርካታ ቦታዎች የድምፅ ቆጠራው ሂደት እንዲዘገይ በማድረግ ለበለጠ ማጭበርበር ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡

ስለሆነም በዛሬው ወቅታዊ መግለጫችን ቀጥለው የተመለከቱትን አቋሞቻችንን እንገልጻለን፡፡

1. ብሔራዊ ምርጫ ቦርድና በየደረጃው የተወከሉት የቦርዱ ምርጫ አስፈጻሚዎች ከምርጫው በፊት፥ በምርጫው ወቅትና ከምርጫው ቀጥሎም ባሉት ሕጋዊ የጊዜ ገደቦች ያቀረብናቸውን የምርጫውን ግድፈቶች ሁሉ ትኩረት ሰጥተው የእርምት እርምጃዎችን ሳይወስዱ ቆይተው ሰሞኑን ይፋ እያደረጉ ያሉትን "ጊዚያዊ  የምርጫ ውጤት" መግለጫዎች የማንቀበላቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡
   የኅብረቱ አባላትና ደጋፊዎች በገዥው ፓርቲ የደረሰባቸውን ከፍተኛ ጫናና አፈና ተቋቁመው ባካሄዱት ተጋድሎ ቀላል ግምት የማይሰጠው ውጤት እንዳስመዘገቡ እስካሁን በእጃችን በሚገኝ ከምርጫ ጣቢያዎች በተገኙ መተማመኛዎች መሠረት የተገነዘብን ቢሆንም እስከ ዛሬ ምርጫ ቦርድ ይፋ በሚያደርጋቸው "ጊዜአዊ ውጤቶች" መሠረት ኅብረቱ ያሸነፈው በጣም ውሱን የሆኑ መቀመጫዎችን ብቻ እንደሆነ ገልጿል፡፡ በዚህ አካሄድ ይፋ ካልሆኑት መቀመጫዎች የዚያኑ ያህል "ተጨማሪ ብንሰጣቸው ይበቃቸዋል" ተብሎ የተገመተ ይመስላል፡፡ ይኸ የሚያመለክተው የገጠሩ አካባቢ እንደቀድሞው ይፋ ማጭበርበርና የኃይል እርምጃ ቢወሰድበትም አሁንም ድምፁን ቢነጠቅ መብቱን ለማስከበር ሳይንቀሳቀስ በዝምታ ያልፋል ተብሎ የተገመተ፥ የተሳሳተ የኢሕአዴግ ካድሬዎች ግንዛቤ መሆኑን ማጋለጥ እንፈልጋለን፡፡

2. ኅብረቱ የተወዳደረባቸው የምርጫ ክልሎች በአብዛኛው የውጭና የአገር ውስጥ ታዛቢዎችና ጋዜጠኞች ባልተገኙባቸው በኦረሚያ፥ በደቡብና በሰሜኑ ገጠር አካባቢዎች መሆኑ ይታወቃል፡፡ ኢሕአዴግም የታጠቀ ኃይሉን አሰማርቶ ገሃድ የወጣ የኃይል እርምጃ የታከለበት ማጭበርበር የፈጸመውም በነዚሁ አካባቢዎች ሲሆን፥ የምርጫ ቦርድ ተወካይ የሆኑት የምርጫ አስፈጻሚዎችም የኅብረቱ ተወካይ


ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሳ.ቁ 18573 አዲስ አበባ ∀ ኢትዮጵያ
P.O.Box 18573 Addis Ababa, Ethiopia
ስልክ ቁጥር (Tel.No) 251-1530945 ፋ#| (Fax)

ሰሜን አሜሪካ (North America)
P.O.Box 73246
Washington DC  20056-3246, U.S.A
(Tel.No) 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

ታዛቢዎች በየምርጫ ጣቢያው እንዳይመደቡ በማገድና የተመደቡትንም በማባረር ኅብረቱ የድምፅ መስጠቱንና የድምፅ ቆጠራውን ሂደቶች እንዳይከታተል በማድረግ ከፍተኛ ደባ የፈጸሙባቸው አካባቢዎች መሆናቸውን በመረጃዎች በማስደገፍ ላቀረብነው አቤቱታ የምርጫ ቦርዱ ፍትኃዊ ምላሽ መስጠት አለመቻሉንና አለመፈለጉን እናወግዛለን።

3. ኅብረቱ በየወቅቱ የምርጫ ግድፈቶች የተከሰቱባቸውን የምርጫ ክልሎች፥ ጣቢያዎችና አካባቢዎችን እስከነተጨባጭ ዝርዝሮችና ማስረጃዎች በየደረጃው ለምርጫ አስፈጻሚዎችና በይግባኝም ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድና ለሚመለከታቸው ሁሉ አቅርቧል። በዚሁ መሠረት ከፍተኛ የምርጫ ግድፈቶች የተፈጸሙባቸው በኦሮሚያ ክልል በ11 የምርጫ ክልሎችና 390 የምርጫ ጣቢያዎች፥ በደቡብ ክልል በ62 የምርጫ ክልሎችና በ31 የምርጫ ጣቢያዎች፥ በአማራው ክልል በ6 የምርጫ ክልሎችና 10 የምርጫ ጣቢያዎች በድምሩ በ79 የምርጫ ክልሎችና በ431 የምርጫ ጣቢያዎች ታዛቢዎች ባሉበት ዳግም ምርጫ ወይም እንደሁኔታው ዳግም ቆጠራ እንዲካሄድ ኅብረቱ ጠይቋል። እንዲሁም በትግራይ ክልል ያቀረብናቸው እጩዎቻችን በሙሉ በመጨረሻው የምርጫ ሳምንት በኃይል ተገድደው ከምርጫው እንዲወጡ ተደርጓል። በነዚህ የምርጫ ክልሎች ላይ ገለልተኛ ታዛቢዎች ባሉበት ዳግም ምርጫ እንዲካሄድ እየጠየቅን፥ እንዲሁም ማሽነፋችንን የሚገልጽ መተማመኛ በያዝንባቸው ክልሎች ላይ ውጤታቸው የእኛ ታዛቢዎች በሌሉበት ተለውጠው የኢሕአዴግን አሸናፊነት እንዲገልጹ መደረጋቸውን ኅብረቱ የማይቀበል መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።

4. የምርጫው ሰላማዊ ሂደት ከተቋረጠበት ከግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ/ም ምሽት ጀምሮ ኅብረቱ በተለያዩ መድረኮች ላይ ከሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በጋራና በተናጠልም ገዥው ፓርቲና የምርጫ ቦርድ በመመሳጠር የምርጫውን ድምፅ ቆጠራ ከማዘግየት እንቅስቃሴአቸው እንዲቆጠቡና ታዛቢዎቻችን ባሉበት ቆጠራው ተካሂዶ ውጤቱ ባፋጣኝ እንዲገለጽ በተደጋጋሚ ቢያሳውቅም ከጥፋታቸው ለመታረም ፈቃደኛ ባለመሆን የምርጫውን ውጤት ለመቀልበስ የሚደረገው ሙከራ በአስቸኳይ እንዲቆም ስናሳስብ ቆይተናል። ስለሆነም የሕዝብን መብት በመርገጥ በሚካሄደው የቅልበሳ ሙከራ ውሳኔው በኃይልና በማጭበርበር የተሻረበት ሕዝብ መብቱን ለማስከበር በሚወስደው አቋም ለሚከሰተው ማንኛውም ሁኔታ ተጠያቂው ራሱ ኢሕአዴግ እንደሚሆን አበክረን እንገልጻለን።

5. ገዥው ፓርቲና ካድሬዎቹ ከምርጫ ዕለት በፊት የኅብረቱን አባላትና ደጋፊዎች ከምርጫ ተሳትፎ ውጭ ለማድረግ በሽዎች ማሰራቸው ሲታወቅ፥ ከምርጫው በኋላም ኅብረቱን ለምን መረጣችሁ በማለት ሕዝባችንን በማሰር፥ በገንዘብ በመቅጣትና በአጠቃላዩም በማሸበር ላይ ይገኛሉ። ይኽ ሁኔታ ከ1992 ዓ/ም ምርጫ በኋላ በደቡብ የተከሰተውን መጠነ-ሰፊ ወከባና በመራጩ ሕዝብ ላይ በገዥው ፓርቲ የተሰነዘረውን የኃይል እርምጃ ያስታውሰናል። ስለሆነም ኢሕአዴግ እርሱን ባልመረጠው ሕዝባችን ላይ መሰንዘር የጀመረውን የቂም በቀል እርምጃ ባስቸኳይ እንዲያቆም አጥብቀን እንጠይቃለን።

6. በመቀጠልም ኅብረቱ ይኽ ጉዳይ ለሚመለከታቸው ማናቸውም ክፍሎች የሚከተለውን መልእክት ማስተላለፍ ይፈልጋል፤

ሀ) ማጭበርበር በሌለበት ፍትኃዊ ምርጫ ኅብረቱ ቢሸነፍ ውጤቱን በፀጋ የሚቀበል መሆኑን ኅብረቱ ለሁሉም ወገኖች ይገልፃል። ስለሆነም የግንቦት ሰባቱ ምርጫ በአመዛኙ ይኸንን መሠረታዊ መስፈርት ሳያሟላ መመጠናቀቁ ኅብረቱ በነፃነት በምርጫው የመወዳደር መብቱ በገዥው ፓርቲና በምርጫ ቦርድ ተወካይ ምርጫ

አስፈጻሚዎች ተጥሏል። ስለሆነም የመወዳደር መብታችን በተጣሰባቸው የምርጫ ክልሎች ሁሉ የተከሰቱትን ችግሮች የሚያጣራ ኅብረቱ የተወከለበት፥ የዓለም-አቀፍና የአገር-አቀፍ የምርጫ ታዛቢዎች ያሉበትና የምርጫ ቦርድ ተጠሪ ያለበት አንድ አጣሪ አካል ተቋቁሞ በጉዳዮቹ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ጥሪ እናደርጋለን።

ለ) ምርጫው እንዳይጭበረበር ከፍተኛ ትግል ላደረጋችሁና ክቡር መስዋዕትነት ለከፈላችሁ አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን ፦
በአሁኑ ወቅት በኃይል እየተነጠቃችሁ ያለውን ድምፃችሁን ለማስመለስ ኅብረቱ በሕጋዊ አግባብ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ አቤቱታ አቅርቦ ጉዳዩን በመከታተል ላይ ይገኛል። ይኸ ሕጋዊ ጥረት ውጤት አልባ የሚሆን ከሆነ በሰላማዊ ተቃውሞ መብታችሁ የሚከበርበትን አካሄድ ከኅብረቱ አመራር ጋር በመቀየስ የነቃ ተሳትፎአችሁን እንድታጠናክሩ ጥሪ እናደርጋለን።

ሐ) ሌሎች የኢሕአዴግ አገዛዝ መርሮአችሁ ለውጥ ለፈለጋችሁ ኢትዮጵያውያን ሁሉ፦
ዛሬ ኢሕአዴግ በተለመደው ማስመሰያ ቋንቋው "ያልመረጣችሁን ሁሉ መልዕ ክታችሁ ደርሶናል፥ ፖሊሲያችን የማይለወጥ ቢሆንም አፈጻጸሙን በማፋጠን ጥቅማችሁን እንጠብቃለንና ከእኛው ጎን ቁሙ..." እያለ ከትግላችሁ ለማዘናጋት እየሞከረ ይገኛል። የሕገ-መንግሥቱን ድንጋጌዎች በመጣስ በአንድ ሰው ትዕዛዝ የአፈና መዋቅሩን በከፍተኛ ሁኔታ ዘርግቶ እያለ "እናንተ ሰላማዊ ናችሁ፥ ነገር ግን ሰላማችሁን ለማደፍረስ የሚሯሯጡ ተቃዋሚዎችን ለመቆጣጠር ጊዜያዊ ማዕቀብ ጥለናል..." በማለት ተቃዋሚዎችንና ደጋፊዎቻቸውን ለመነጣጠል ሙከራ እያደረገ ይገኛል። ስለሆነም የገጠርና የከተማ ሳትባባሉ፥ አንዱ ለሌላው ጥቃት በአንድ ላይ በመቆም የምርጫው ውጤት በሕጋዊ አግባብ ሁሉንም በሚያስማማ ሁኔታ እስከሚቋጭ ድረስ በሰላማዊ ትግላችሁ እንድትቀጥሉ ኅብረቱ ጥሪ ያደርጋል።

መ) የአገር-ውስጥና የዓለም-አቀፍ የምርጫ ታዛቢ ቡድኖች፦
በአንፃራዊ መልኩ ዴሞክራሲያዊ ሆኖ የተጀመረው የምርጫ ሂደት በአሁኑ ወቅት የገባበትን አጣብቂኝ የተገነዘባችሁ ይመስለናል። ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄዱ የሁለት ምርጫዎች ውጤት የተጭበረበረ እንዲሆን አስተዋጽዖ ያደረገው የምርጫ ቦርድ መዋቅር ሳይለወጥ የአሁኑም ምርጫ ነፃ እንደማይሆን ተቃዋሚዎች አምርረው የታገሉበትን ምክንያትም አሁን የተገነዘባችሁ ይመስለናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የዴሞክራሲ ፅንሰ-ሃሳብ ግንዛቤው አምባገነን ገዥዎች የሥልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም እንደሚያስወሩት "ጅምር ላይ" ያለ ሳይሆን ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑንም ተገንዝባችኋል። ስለሆነም ኢትዮጵያ በ21ኛው ክፍለ-ዘመን ዴሞክራሲን በቃል እንጅ በተግባር በማያውቁ ብልጣብልጥ አምባገነኖች እጅ ወድቃ ዘለዓለም በድህነት ስትማቅቅ እንዳትኖር የጀመራችሁትን ጥረት በጽናት በመቀጠል በኃይል የተጨናገፈው የምርጫ ሂደት በሰላምና በሕጋዊነት እንዲጠናቀቅ፥ ግድፈት በተፈጠረባቸው የምርጫ ክልሎች ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ በገዥው ፓርቲና በምርጫ ቦርድ ኃላፊዎች ላይ ተገቢውን ጫና ለማሳረፍ በአጣሪ አካሉ ውስጥ በመሳተፍ ምስክርነታችሁን እንድትሰጡ ኅብረቱ አበክሮ ይጠይቃል።

ኢሕአዴግ የከተማውን ማዕበል በዓይኑ በማየቱ በከተሞች አካባቢ አደብ ገዝቶ ከሆነ የገጠሩ ማዕበል ከተነሳ መመለሻው ጭንቅ እንደሚሆንም መገንዘብ ይኖርበታል። ዛሬም እንደቀድሞው በትግሉ መድረክ ላይ ብቅ ያለውን በተናጠል እየመታሁ እቀጥላለሁ የሚል እምነት ካለው ዛሬ ሕዝባችን በአንድ ቃል ተማምኖና "የግፍ አገዛዝ በቃኝ" እንዳለ ማወቅ ትይኖርበታል። ለጥቅማቸው ያደሩ ውር ውር የሚሉ ጥቂት ደጋፊዎቹ ውሳኔውን በተነጠቀው ሕዝብ ማዕበል ፊት ቆመው እንደማይመክቱት ማወቅ ይኖርባቸዋል።

በመጨረሻም እስካሁን ድረስ በኅብረቱ በኩል በምርጫው ላይ በኢሕአዴግ የተፈጸመውን ደባ በሕጋዊ  መንገድ ለማሳረም በመሻት የሕዝቡ የቁጣ ስሜት ገንፍሎ እንዳይወጣ ባለበት ሃላፊነት የሚያረጋጉ መግለጫዎች መስጠታቸው የደጋፊዎቹን ድምፅ ለመስረቅ አመች ሁኔታ የተፈጠረ ተደርጎ የተወሰደም ይመስላል፡፡ ይኸ የተሳሳተ የኢሕአዴግ  ግምት መሆኑን የወደፊት የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ሰላማዊ እንዲሆን ለሚመኙና ሃላፊነት ለሚሰማቸው ወገኖች ሁሉ ዛሬ በዚህ መግለጫ አበክረን መግለጽ እንወዳለን፡፡

ሥልጣን የሕዝብ መሆኑን ለአምባገነኖች ለማሳየት ያለፍርሃት በኅብረት እንነሳ!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)

ግንቦት 22 ቀን 1997 ዓ/ም
አዲስ አበባ